# መንግስታዊ ሽፍጥና ደጋፊዎቹ

የብልፅግና ፓርቲና የአብይ አህመድ አፍቃሪዎች የ"Stockholm syndrome" ተጠቂዎች ይመስሉኛል ፣ብየ ለማለት የስነልቦና ባለሙያ ባለመሆኔ ባልደፍርም በአገራችን በተረት መልስ የሚነገረው "የፈሪው ሰው" አገላለፅ ይገልፃቸዋል ለማለት ግን እደፍራለሁ። ፅሁፉ በስርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑትን ሆድ አደሮችና በዘር ልክፍት የተለከፉትን ፅንፈኞች አይመለከትም።

በነገራችን ላይ Stockholm syndrome በአለም ላይ ያሉ የስነ አእምሮና የስነ ልቦና ባለሙያዎች የሚጠቀሙት ቃል ነው። "Stockholm syndrome" ን በጥቅሉ ወደ አማርኛ ብመልሰው እ. ኤ. አ. በ1973 ዓ ም በስቶክሆልም ከተማ በአንድ የባንክ ዝርፊያ በተያዙ ሰዎች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩት የስነልቦና ባህሪያትን ለመግለጽ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው፣ ሁለት ዘራፊዎች የጦር መሳሪያ ይዘው ባንኩ ውስጥ ገብተው አራት የባንክ ሰራተኞችን ለ 6 ቀናት ያህል አግተው፣ በሰላም መኖር የለመዱት ታጋች የባንክ ሰራተኞች በፍርሀት፣ በጭንቅና በስቃይ ስድስት ቀን ይከርማሉ። በመጨረሻም ነፃ ሲወጡ፣ ከፍርሀታቸው የተነሳ ወንጀለኞቹ እንዳይጠየቁ አዎንታዊ ስሜትን ያዳበሩና እንዲያውም ለእነሱ ርህራሄን ያሳዩበትን የተጠቂዎቹ የስነ ልቦና ቀውስ ነው።

ሌላው ልጅ ሆኘ ከሰማሁት ተረት ውስጥ የማስታውሰው የፈሪው ሰው ታሪክ እንዲህ ነው። ሶስት ሰዎች ለንግድ ወደ ሩቅ አገር ይሄዳሉ። ቀኑን ሙሉ ሲጓዙ ውለው በአጋጣሚ አንድ ምሽት መንደር በሌለበት ቦታ ማደር ግድ ይሆንባቸዋል። ለመተኛት ሲዘጋጁ ፈሪው ሰው እባካችሁ እኔን ከመካከላችሁ አስተኙኝ ይልና ይጠይቃል። ጓደኞቹ በጥያቄው ተስማምተው ፈሪው ሰው በመካከላቸው ይተኛል። ታዲያ ፍርሀት ብቻውን መፍትሄ አይደለምና ሌሊት ከተኙበት ጓደኞቹ የሆነ ነገር ሲንኮሻኮሽ ሲሰሙ ምንድነው የሚንኮሻኮሸው ብለው ሲጠይቁ እመሀል የተኛው ፈሪ ድምፁን ቀነስ አድርጎ "ዝም በሉ ጅብ የእኔን እግር እየበላ ነው" አለ ይባላል።

ምንም እንኳን ይሄን ተረት ልጅ እያለሁ ብሰማውም ዛሬም እግሩን ጅብ እየቆረጣጠመው ዝም በሉ ብሎ በፍርሀት ከተበላው ፈሪ ሰው ባልተናነሰ በበደሉ መሀል በደስታ የሚቧርቁ ስዎች ይታያሉ። ከመጠን በላይ በፍርሀት ተውጠው በገሀዱ አለም የለውን፣ የሚሆነውን የሚፈፀመውን በማንነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት መቃወሙ ቀርቶ ጥቃት እየተፈፀመ ነው የሚሉትን የሚከላከሉ አገር ወዳድ ዜጎች መኖራቸው ያሳዝናል።

አጋቾችና ጥቃት ፈፃሚ የኦሮሞ ፅንፈኞች የሚያደርጉትን ስለሚያውቁ ጥቃት የሚፈፅሙት ተደራጅተው ነው። ልብ የሚሰብረው ነገር ግን ጡታቸው እየተቆረጠ የተገደሉት፣ ከፎቅ ተወርውረውና በስለት ተጨቅጭቀው የተገደሉት ላጋ ባለተስፋ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በትውልድ አማራ በመሆናቸው ሁኖ ሳለ የተጠቂዎቹ ወገኖች አማራ ተጠቃ ማለትን እንደ ዘረኝነት ይቆጥሩታል። ዘረኝነትን መጠየፍ አግባብ ቢሆንም ሌላው ቢቀር እነዚህ እንኳንስ ባለ ሜንጫ አረመኔ ጠላት በአገራቸው ይኖራል ብለው ቀርቶ ከትምህርታቸውና ከወደፊት ተስፋቸው በቀር ቅራኔን ማስተናገድ እንደሚጠብቅባቸው እንኳን የስነልቦና ዝግጅት ያላደረጉት፣ ስለፖለቲካ ምንም ግንዛቤ የሌላቸው፣ የገበሬ ልጆች ብርድ ፀሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው በጭራሮ ዳስ ውስጥ ተምረው በኩራዝ እያጠኑ ለዚህ የደረሱትን በጅምላ የታገቱት ተማሪዎች መንግስት ጆሮ ዳባ ልበስ ባለበት ሰዓት ማን ይድረስላቸው? ማን ይታደጋቸው?

ውሸት የማይታክተው መንግስታችን የታገቱትን ተማሪዎች አስለቀቅን ካለ ሳምንታት ተቆጠሩ፣ ልጆቹ የውሀ ሽታ ሆነው ቀሩ እንጅ። ከሰፈራቸው በቀር ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደው የማያውቁ ወላጆች፣ ምርጫ ቢያጡ፣ በሌለ አቅማቸው ያላቸውን አሟጠው፣ ተበድረውና ተቀድመው ወረዳ፣ ክልል፣ ዩኒቨርስቲ፣ አገር እያካለሉና እየተንከራተቱ መንግስት ጋር አቤት ቢሉም ሰሚ አላገኙም። የነገ ብሩህ ተስፋ ወጣት ተማሪዎችን እያስቀጠፈ ችግኝ ተክሎ ውሀ ሲያጠጣ በፎቶ የምናየውና ስለ ብልፅግና ትንታኔ የሚሰጠው ባተሌ መሪያችንም ስራ ስለሚበዛበት ባይሰማ ይሆናል አንዳች ነገር አልተነፈሰም።

የፈረደባት እናትማ ምስኪን አቅመ ደካማ ናት። ዘጠኝ ወር አርግዛ አምጣ ወልዳ በጎስቋላ ኑሮ ያሳደገቻቸው ልጆች በአረመኔ እጅ ወድቀው፣ ይሙቱ ይዳኑ ሳታውቅ በድጋሚ ሰቆቃ አርግዛ ቀንና ሌሊት ምጥ ላይ ናት።

ብርጋዴል ጀኔራል አሳምነው ፅጌ በትንቢት መልክ በአደባባይ በህዝብ ፊት "አሁን የገጠመን ፈተና ከዛሬ 500 ዓመት በፊት ከገጠመን ፈተና የከፋ ነው " ብሎ ነበር። ግን ምን ያደርጋል እንደፈራው ተረኞቹ ቀደሙና ተስፋ የተጣለባቸውን በተቀነባበረ መንገድ በአንድ ምሽት ጠራርገው አጥፍተው አንዱን የገዳይ አንዱን የሟች ወገን አድርገው አማራን ለመከፋፈል እየጣሩ ነው ፣

ለውጥ ተብየው፣ የተጭናገፈው ወይም የተረኞቹ ለውጥ ከመጣ በኋላ በአገራችን ኢትዮጵያ ስለሚፈፀመው ግፍ፣ ስለበደሉማ ምን ቃላት ይገኝለታል። በአብይ አህመድ ዘመን የሚደረገውን በርካታ የፓለቲካ ሸፍጥ ሳንቆጥር፣ ከሚፈፀመው አይን ያወጣ በደልና አረመኔዊ ተግባር ከብዙ በጥቂቱ እነሆ፣

- በአማራ ክልል ተብየው ውስጥ ከወያኔ የቀጠለ ተግባር፣ ህዝብ እርስ በርሱ በጎጥና በሀይማኖት ተጣልቶ እንዲጫረስ የሚደረግ ርብርብ አሁንም እንደቀጠለ ነው።
- ትናንት በሀረር ከተማ የጥምቀት በዓል ሲከበር ወደ ቤተክርስቲያን ሲተኩሱ የነበሩት የመንግስት ፓሊሶች እንደነበሩ የአይን እማኝ ከሆኑት በፁእ አባታችን አቡነ ማቃሪዮስ ሰምተናል።
- በአሁኑ ጥምቀት በዓል ላይ ሰንደቅ አላማ ከቤተምንግስቱ ጎረቤት ከቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን አዲስ አበባ ያወረደው የመንግስት ታጣቂ መሆኑን ልብ ይሏል።
- መንግስት አንቀባሮ ጠባቂ መድቦ የሚያስጠብቀው አሜሪካዊ ዜጋ ጀዋር ሙሀመድ ጨፍጭፉ ብሎ ያነሳሳቸው ቄሮዎች ቄሮዎች በሜንጫ እየቆራረጡ በዲንጋይ እየወገሩ ሲጥሉ አይተናል። የጨረሱት ህዝብ መንግስት እንኳን ባመነው ቁጥሩ 86 ነው።
- ቄሮዎች የገደሉትን ሰው ቆራርጠው እየጣሉ ቤተዘመድ ቀብር ለመፈፀም የጎደለ አካል አፅም በማፈላለግ ሲሰቃዩና ጎደሎ አስከሬን ሳይቀበር ሲሰነብት አይተናል ሰምተናል።
- ሻሸመኔ ላይ የሰው ልጅ ህዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በአሰቃቂ ሁኔታ ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ ተገድሏል።
- በቡራዩ አንፎ፣ አሸዋ ሜዳ በተደረገ ወረራ ዘርን መሰረት በማድረግ ነዋሪዎች የደረሰባቸው ኢሰብ አዊ ጥቃት፣ አሰቃቂ ጭፍጨፋ፣ የሴቶች፣ ህፃናትና ነፍሰጡር ሳይቀር መደፈር፣ ከማናችንም አእምሮ የማይፋቅ ጠባሳ ጥሎ እንዳለፈ የሚታወስ ነው።
- አዲስ አበባ ዙሪያ ከባሌ ከአርሲ ከአንቦ ሀረር በ አጠቃላይ ከኦሮሞ ክልል ተብየው የተፈናቀሉ ሰዎች ስቃይ እንግልትማ ቤት ይቁጠረው።
- ወለጋ አካባቢ ሁለት ቀናት ብቻ በሁለት የተዘረፉት ባንኮች 17 መድረሱን የየአካባቢው ባለስልጣናት እንተናገሩም እናስታውሳለን።

ዛሬም ታዲያ በዚህ ሁሉ አሰቃቂ በደል የሚሰቃይ ህዝብ ብሶት ኮርኩሮን በደል አለ ብለን ስንጮህ አንዳንዶቹ ፈሪ ተደማሪዎች እውነት ጋር መጋፈጡ ሲከብዳቸው፣ በፍርሀት አብይ አህመድንና ብልፅግናን በመደገፍ የሚመጣውን መከራ ለመከላከል በማሰብ፣ ማንን አዘጋጅታችኋል? የከፋ ነገር እንዳይመጣ! ብለው ያስፈራራሉ። "አብይ አንድ ሰው ነው፣ ሚሊሻ አይደል! ምን ማድረግ ይችላል?" በማለትም መንግስት መጠየቅ እንደሌለበት ሲጠቁሙና ሲከላከሉ ይታያሉ። እነዚህ አብይን አትንኩ የሚሉ የጭፍን ደጋፊዎች ይህ ሁሉ በደል የሚፈፀመው በኦሮሞ ላይ ቢሆን ምን ይከተል ነበር ብለው ማሰብ አይፈልጉም።

ካቢኔውን ግማሽ በግማሽ በሴት ሚኒስትሮች ያስታጠቀው የቀድሞው ኢህአዴግ የአሁኑ የብልፅግና መንግስት ከደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ ታፍነው በምድር ላይ ያለው ሁሉ ግፍ የሚፈፀምባቸው ቁጥራቸው በርከት ያለ ሴት የአማራ ተማሪዎችን እንኳን ሊታደጓቸው ቀርቶ ተማሪዎችን አስለቀቅን ብሎ የተዛባ መረጃ በመስጠት አፋችሁን ዝጉ እያሉና በአሰቃዊው መከራ እያፌዙ ነው።

ዶክተር አብይ በበአለ ሹመቱ ስለእናቱም ሆነ ስለሚስቱ ሲናገርና ስለ ቀደሙት ጀግኖች መሪዎች ሲተርክ ቀልብ በመሳቡ ብዙዎቻችን ኢትዮጵያ ሰው አገኘች መስሎን ነበር።

ነገር ግን ዶክተር አብይ ተሽሞንሙኖ በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ እያለ በአማርኛ የሚያዘንበው ሚዛን የማይደፋ፣ ባዶ ቃል እንደሆነ በተደጋጋሚ ያይቷል። አሁንም ዶክተር አብይ በተደጋጋሚ እኔ "ደማሪ፣ አበልፃጊ" ነኝ ብሎ በተናገረው ልክ በተግባር ሳያሳይ እየተወደሰ የዚህ አይነት አሰቃቂና አሳፋሪ በደል ከተፈፀመ ነገ ተቃውሞው ሲበረታ ምን ሊፈጠር ይችላል ብሎ ማሰብም ግድ ይላል።

ግን ትዕግስት እስከ መቼ፦ እንደተባለው ጠቅላዩ ከአቅሙ በላይ ከሆነው ወደ ኢትዮጵያዊው ፊቱን አዙሮ እውነት እውነቱን ተናግሮ መመካከር ነበረበት እንጅ ሴት እየተደፈረ፣ ቤተ እምነት እየተቃጠለ፣ ተማሪዎች እየታገቱ ጠዋት ማታ ብልፅግና ቢል ምን ፋይዳ አለው? መከረኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ከመንግስት ልዩ ጥቅም አልጠየቀም። የህዝቡ ምኞትና ፍላጎት በድህነቱ ሳልፈናቀል፣ ሳልገደል፣ ሳልሰጋ የሰውነት መብቱ ተከብሮና በሰላም እንድኖር መንግስት የመንግስትነት ድርሻውን ይወጣ ብቻ ነበር።

እነዚህ እያንዳንዱን ነገር አብይ አልፈፀመም፣ አብይ ሚሊሽያ አይደለም ብለው ሽክሙን ከአብይ አህመድ ላይ ለማቅለል ለሚጥሩት እኛምእያልን ያለነው አብይ ከሌለበት፣ በአደባባይ "ኦሮሞን ኦሮሞ አይገልም፣ አይተናኮልም" ያለውን በተግባር እያዋለ ካልሆነ፣ኢ-ሰብአዊውን ድርጊት የሚቃወም ከሆነ በአቅም ማጣት ብቻ ህግ ማስከበር ስላልቻለ ስልጣኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስረክብ ነው።

ከሞት ተከላከለን፣ ከጥቃት ታደገን፣ የሰው ልጅ እንደልቡ ገብቶ ይውጣ፣ ሀይማኖት የግል ነውና ቤተ እምነቶች ይከበሩ ለሚሉት ጥያቄዎች አግባብ ያለው መልስ መስጠት የማይችል መንግስት ስልጣኑን ለሽግግር መንግስት ማስረከብ አለበት እንጅ ህዝብን በፍርሀት ቆፈን አፍኖ የዘር ማጥፋትና የዘር ማፅዳት አጀንዳውን ማስቀጠል አይችልም።አባቶቻችን ለድል የበቁትና አሁን አንገታችንን ቀና አድርገን እንድንሄድ ያደረጉን በፍርሀት ሳይሆን ተደራጅቶ ጠላትን በመጋፈጥ መሆኑ ለደቂቃም ቢሆን መረሳት የለበትም።

ዘውዲቱ የማነ

2020-01-27

zewdituy@gmail.com